# ቁጥር - ፪

# የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር።

*የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የወደቀችበትን ፈተና ባለፈው ቁጥር ፩ ገልጸን ተከታዩን ጽሑፍ ሰ.ጉ.አ በሚቀጥሉት 2-3- ሳምንት የሚሰጠውን ምላሽ አይተን እንመልሳን ብለን ነበር። ነገር ግን የሰ/አ/ጉ አባላት ድርጊቱ ስላሳፈራቸውና መልእክቱ ትክክለኛ መሆኑን ስላመኑበት ምላሽ ሊሰጡ ባለመቻላቸው ቃላችንን ጠብቀን ይህን ቁጥር ፪ ጽሑፍ ከበቂ ማስረጃዎች ጋር ይዘን ቀርበናል።*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ፈሪሳውያን እንዴት አድርገው በነገር ከቄሣር ጋር እንደሚያጣሉት ተማክረው ለቄሣር ግብር መስጠት ተፈቅዶአልን ወይስ አልተፈቀደም? በማለት ጠየቁት። ኢየሱስም ክፋታቸውን አውቆ ፤ እናንተ ግብዞች ፥ ስለ ምን ትፈትኑኛላችሁ? የግብሩን ብር አሳዩኝ አለ። እነርሱም ዲናር አመጡለት ፤ እርሱም ይህች መልክ ጽሕፈቲቱስ የማን ናት? አላቸው። የቄሣር ነው አሉት። በዚያን ጊዜ እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ አላቸው (ማቴ፡-22 ፤15-22)። በተጨማሪም በዚሁ በማቴዎስ ወንጌል ላይ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም ፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል ፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል ፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም (ማቴ፡-6 ፤24)። እንግዲህ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ስለ ገንዘብ ቢሆንም ፤ ይህ የጌታችን መልስ ወይም ትዕዛዝ በእርሱ ደም የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን እንዴት መንፈሳዊ ሕይወት ሊኖራት እንደሚገባና ከዓለማዊ አመራር ልትርቅ ጭምር እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል።

ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት በመጀመሪያ መመረጥ ያስፈልጋል። የአምላካችን ፈቃድ እንዲሆንም በጸሎት መጠየቅና ራሳችንን ለእርሱ ለማስገዛት ፍፁም ዝግጁ መሆን አለብን። ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩ ካህናትም ሆኑ ሌሎች ሰዎች ሁሉን እኩል እንዲያዩ ፣ ምዕመናኖቻቸውን በፍቅር እንዲጠብቁ እንዲንከባከቡ ነገር ግን መንጋዎቹን ለሚያጠፉና ለሚበትኑ እረኞች ወዮላቸው! ይላል እግዚአብሔር (ትን ኤር 23፡-1)። መንጋዎቿን ትጠብቃለች ሲባል ፤ የክርስትና እምነትን አምነው ለሚመጡ አስፈላጊውን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ትፈጽማለች ፤ ምዕመናኖቿ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ታንፀው እንዲወጡ ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን ትፈጽማለች ፤ ሲሰደዱ አብራ ተከትላ ባሉበት ታጽናናለች ፤ ግፍ ሲፈጸም ታወግዛለች ወዘተ። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲያስተምር ሳለ እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ፥ ወደ እኔ ኑ ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ ባለው መሠረት ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን አምላካችንን አምኖ ለመጣ ለማንኛውም ሰው በሯ ክፍት ነው (ማቴ 11፡-28)።

የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን በብዙዎች ዘንድ *The unifying factor* በመባል ትታወቃለች። ምክንያቱም ከተለያየ ጎሣ እና የፖለቲካ ድርጅት የመጡ ሁሉ በእርሷ ስለሚሰባሰቡ ማለት ነው። ሁሉንም የሚያሰባስባቸው ደግሞ በአደባባይዋ የሚሰበከው ፤ ቃለ እግዚአብሔር ፣ ፍቅርና አንድነት ስለሆነ ነው። የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ከሀገር ቤት አልፋ በውጭ ዓለም የተበተኑትን መንጋዎቿን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲጎለምሱ ማድረግ ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል። ከእነዚህም አብያተ ክርስቲያናት

እንደ የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ናት። ይሁን እንጂ በውጭው ዓለም ያለችው ይህች ቤተ ክርስቲያናችን ይህንንም ብትከተልም ፤ አንዳንድ የተለያየ ፍላጎትና ዓላማ ያላቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያኒቷን መጠቀሚ ለማድረግ ሲፈልጉ ግጭቶች እየተፈጠሩ እስከ አሁን አለን።

እ.አ.አ በ1990 አካባቢ ቤተ ክርስቲያናችን በቤዝ ዎተር በነበረችበት ወቅት ፤ የእንግሊዝ መንግሥት ስደተኞችን ከሀገር ሊያስወጣ ነው ስለዚህ ኮሚቴ ተቋቁሞ መቃወም አለብን የሚል ሐሳብ ከአንዳንድ ሰዎች መጣ። በዕለቱ የተካሄደው ስብሰባ የተበተነው በፍፁም ረብሻና አለመግባባት ሲሆን ፤ ሁለተኛ እንዲህ ዓይነት ሰውን የሚከፋፍልና የሚረብሽ የፖለቲካ ይዘት ያለው ስብሰባ በቤተ ክርስቲያኗ እንዳይካሄድ በተጨማሪም ምንም ዓይነት የፖለቲካ ይዘት ያለው ማስታወቂያ እንዳይነገር የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ወሰነ። ይሁን እንጂ ችግሮች መልካቸውን እየቀየሩ መምጣታቸው አልቀረም። በዚያው በቤዝ ዎተር እያለን ጥቂት ሰዎች የዐፄ ኃ/ሥላሴ አፅም ስለተገኘ ጸሎተ ፍትሐት ይደረግልን ብለው ጠይቀው ነበር። ቤተ ክርስቲያንም አገልግሎቷን ለጠየቀ ሁሉ ስለምትፈጽም በጥያቄው መሠረት ፈቃደኝነቷን ገለፀች። ይሁን እንጅ ጠያቂዎቹ ከጸሎተ ፍትሐቱ ፍጻሜ በኋላ ስለ ዐፄ ኃ/ሥላሴ የሕይወት ታሪክ እዚያው ቤተ ክርስቲያኗ ውስጥም ማንበብ እንፈልጋለን በማለታቸው በወቅቱ የነበረው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ውይይት አድርጎ በድምፅ ብልጫ ፈቅዶ ነበር። ነገር ግን በዕለቱ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ የተነገሩት ቃላት ፖለቲካዊ ይዘትና አንዱን አክብሮ ሌላውን የሚያወግዝ ስለነበር ብዙውን ሰው ያሳዘነና ለወራት የከተማው ወሬ ሆኖ ሰንብቶ ነበር። የሰበካ አስተዳደር ጉባኤም በተፈጠረው ቅሬታ ሁለተኛ እንደዚያ ዓይነት ድርጊት እንዳይፈፀም ወሰነ።

ወደ ሜይ ፌይር ከገባን በኋላም በአረመኔው ወታደራዊ ደርግ ለተጨፈጨፉት 60 ሚኒስትሮች ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ ተመሣሣይ ጥያቄ ስለቀረበ ጸሎተ ፍትሐቱ ተፈጽሟል። ይሁን እንጂ አሁንም ካለፈው ስሕተት ባለመማር የስማቸው ዝርዝር መነበብና ሌላም በመባሉ በወቅቱ ከፍ ያለ ቅሬታ ፈጥሮ ነበር። ከዚያም በኋላ አባ ጳውሎስ ወደ ለንደን ቤተ ክርስቲያናችን በመጡበት ወቅት በተፈጠረው ረብሻ በቤተ ክርስቲያችን ለሳምንታት ተዘግታ ግልጋሎት ተቋርጦ ነበር። እንዲሁም ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/አማኑኤል ወደ ለንደን መጥተው ከአንዳንድ ካህናትና ምዕመናን ጋር በመሆን ቤተ ክርስቲያናችን ለመንጠቅ ያደረጉት ሙከራ በጠቅላላው ምዕመናን ከሸፈ። አሁን ወደ አለንበት ባተር ሲ ከገባን በኋላ ቀደም ብለው የተፈጠረውን ችግሮችና እንዲሁም በወቅቱ እየተፈጠረ የነበረውን አለመግባባት በማየት ሁሉም ማኅበረ ካህናትና ምዕመናን የተስማማበት ፤ የሕግ አርቃቂ ኮሚቴ ተቋቁሞ ከዚህ ሀገር ጋር የሚሄድ ሕግ ተዘጋጅቶ ቤተ ክርስቲያናችን በእሱ እንድትመራ የሚል ነበር። በውሳኔው መሠረት 12 ሰዎች ያሉበት ኮሚቴ ተቋቋሞ ፤ሕጉን አርቅቆ ሁሉንም አባላት አወያይቶ በመጨረሻም በማኅበረ ምዕመናኑ እ.አ.አ በ2006 ጸድቆ አገልግሎት ላይ ለመዋል በቀቷል።

ሁሉ ነገር እንደ ሕጉ እየተሠራ እያለ በአገልግሎት ላይ ያለው ኮሚቴ 3 ዓመት ሲጨርስ ባቀረበው ሪፖርት ላይ የቤተ ክርስቲያኒቷ ግዢ ሊፈፀም ስለተቃረበ ክፍያው እስኪያልቅ ይራዘምልን ብሎ ጠይቀው ተፈቅዶላቸው ነበር። ነገር ግን ክፍያውን ከአራት ወራት በኋላ ቢያልቅም ፤ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ እስካሁን ከ2 ዓመታት በላይ በሥልጣን ላይ ይገኛል። በአጠቃላይ ስለ ተጣሰው ሕግ ቁጥር ፩

ላይ የተጻፈውን ያንብቡ (1)። ይኼ የሚያመለክተው ኢትዮጵያውያን ስንባል ከዕድር ሰብሳቢ ጀምሮ እስከ ላይ ድረስ ያለው ምንም ዓይነት ሥልጣን ከተሰጠን ፤ የአገልግሎት ጊዜያችን ሲፈጸም በሰላም አስረክበን ከመሄድ ይልቅ በጥብጠን ወይም አቅሙ ካለን ኃይል ተጠቅመን የመቆየት gene በውስጣችን እንዳለ ነው። እንግዲህ እዚህ በሰለጠነው ዓለም ላይ እያለን ፤ መንግሥታት ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባላት እንዴት ሥርዓት አክብረው ጊዜያቸውን ፈጽመው እንደሚወርዱ እያየን ፤ እኛ ግን ልክ እንደ ሀገር ቤት ወይም አፍሪቃ ምድር ላይ እንደሚታየው ሥልጣን ላለመልቀቅ በተለይ ደግሞ ሌላ ሥጋዊ ጥቅም ለማይገኝበት ለሰ/አ/ጉባኤ አባልነት እንዲህ ከተጋደልን ፤ ይህ በጣም አስደንጋጭና አሳሳቢ ጉዳይ ነው። *ይህ የሚያሳየው የጂኦግራፊ ለውጥ እንጂ ፤ በአስተሳሰባችን እስከአሁን ከገጠሪቷ ኢትዮጵያ እንዳልወጣን ነው። እንዲያውም በገጠሪቷ ኢትዮጵያ ያሉት እንዲህ ዓይነት ዐይን አውጣ ሥራ ይሠራሉ ብዬ አልገምትም።* የሰ.ጉ.አ እንዲህ ሥርዓተ አልበኛ የሆነው ፤ በፖለቲካው ጨዋታ ብዙም ያልተሳካላቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያኗን ለሚፈልጉት ዓላማ ለመጠቀም ከበስተኋላ ሆነው አለንላችሁ እያሉ የልብ ልብ ስለሰጧቸው ነው። እንግዲህ ይህ ሥርዓተ አልበኝነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥቂቱ የታመነ በብዙ ይሾማል (ማቴ 25 ፤14-31) ከሚለው ጋር ሲነፃፀር ፤ በዚህ ነፃ በሆነ ሀገር ላይ ለዚች አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነት ሤራ ከተካሄደ ፤ እነዚህ የሰ.ጉ.አ አባላት ወይም ፖለቲከኞች ወደፊት ሀገር እንመራለን ብለው የሚያስቡ ከሆነ ፤ ሌላ ዕጩ አምባገነኖች እዚሁ እያየን ነው ማለት።

ይህን ሥርዓተ አልበኝነት በመቃወም የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴም (አባላት- መሪጌታ መርሐ ጽድቅ ፣ ልዑል ሚካኤል መኮንን ፣ ሊ/ዲ ዳዊት ድንበሩ እና ብ/ጄነራል ኃይሉ መረዋቅ)እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ9/11/09 7 ነጥብ የያዘ የወቅቱን ችግሮች ዘርዝሮ ሥራውን ማጠናቀቁንና ያለው የሰ.ጉ.አ ሕጋዊ እንዳልሆነ ገልጸው ሥራቸውን ለቀዋል (2)። ከተዘረዘሩት ችግሮች አንዱ የገንዘብና ንብረት አያያዝ የተመለከተ ነው። የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ አባል የሆነው መሪጌታ መርሐ ጽድቅ ከአቶ ጌታቸው በሻውረድ ጋር ሆነው ሂሳብ ሲያጣሩ የሂሳብ አሠራሩ ብዙ ችግር ስለነበረበት ፤ የውጭ ኦዲተር እንዲሠራውና ከዚያ እንደገና አብረው አይተው ሪፖርት ሊቀርብ ተስማምተው ሳለ የ/ሰ/አ/ጉ በድንገት ሂሳቡ ተጠናቋል ብሎ ለጠቅላላው ጉባኤ ሪፖርት አቅርቦ ፤ ሪፖርቱን ከፈለጋችሁ ቻሪቲ ኮሚሽን ሄዳችሁ ጠይቁ በማለት ስብሰባውን ዘግተዋል። በጉባኤውም ላይ የነበሩት መሪጌታ መርሐ ጽድቅ ይህ ትክክለኛ አሠራር አይደለም ብለው ጥያቄ በማቅረባቸው ጭራሽ የ/ሰ/አ/ጉባኤው በመሪጌታ መርሐ ጽድቅ ላይ እርምጃ ወሰዷል (3)። የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴም በኅዳር 12 ቀን 2001 የ/ሰ/አ/ጉባኤው በመሪጌታ መርሐ ጽድቅ ላይ የወሰደው እርምጃ ስሕተት እንደሆነና የሂሳብ ሪፖርቱ በውስጠ ደንቡ መሠረት (አንቀጽ 6(7) እና አንቀጽ 28(11)) እንደሚያዘው በቁጥጥር ኮሚቴ እንዳልቀረበ ፤ በዕለቱ የውጭ ኦዲተር የተባለው የ3 ደቂቃ ንግግር ከማድረግ በስተቀር የሂሳብ ዝርዝር ሳያቀርቡ ከዚህ ቀደም እንደሚደረገው ስለ ሂሳቡ ሳይጠየቁና አባላቱም የሂሳቡ ሪፖርት ትክክል ስለመሆኑ ተወያይትው ሳያጸድቁት የተካሄደው ጉባኤ ሕጋዊ እንዳልነበርና ተጨማሪ የታዩ ችግሮችን ዘርዝሮ ውሳኔውን ለ/ሰ/አ/ጉባኤው አስተላልፏል(4)።

የ/ሰ/አ/ጉባኤው በመሪጌታ መርሐ ጽድቅ ላይ የወሰደው ዓይነት ፍርደ ገምድል አሠራር እንዲሁ በዲያቆን ድርሻዬ ላይ ወስዷል። ዲያቆን ድርሻዬም ለተዘረዘረበት ውንጀላ አስፈላጊውን መልስ ሰጥቷል (5)። የቤተ ክርስቲያኗ ካህናትና ምዕመናንም ይህ እየተደጋገመ የመጣውን የ/ሰ/አ/ጉባኤ ብልሹ አመራርና ፤ በማን ይነካኛል ባይነት ከተፈቀደለት ጊዜ 2 ዓመት አሳልፎ ፤ ከዚያ አልፎ ተርፎ በአገልጋይ ካህናት ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ስላሳሰባቸው ጥር 4 ቀን 2003 ለወቅቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ለአባ ግርማ እየተጣሰ ያለውን ሥርዓት አልበኝነት በአስቸኳይ አንድ እልባት እንዲያገኝ የሚል 6 ነጥብ የያዘ ማሳሰቢያ ፤ ያለበለዚያ ግን በሕግ በኩል እንደሚጠየቁ ፈርመው ደብዳቤ ሰጥተዋል(6)።

ከላይ ጥያቄውን ካቀረቡት የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋይ መካከል አንዱ የሆኑት ቄስ ሙሉ ብርሃን አሁን ደግሞ በዚህ ሳምንት ግንቦት 27 ቀን 2003 ከ/ሰ/አ/ጉባኤ በተጻፈ ደብዳቤ ከአገልግሎት ታግደዋል(7)። ደብዳቤው "….የካህናትና የጥምር ጉባኤ አባላት ያወጣውን የሥራ መመሪያ እንዲቀበሉ ይላል …" እዚህ ላይ ማስተዋል የሚያስፈልገው ማንም እንደሚያውቀው እነዚህ ኮሚቴዎች ከፈረሱ 2 ዓመታት በላይ ሆኗቸዋል ነገር ግን ውሳኔያቸውን በሌለው ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ እንደዚህ ዓይነት የሚያምታታ ዐረፍተ ነገር ጨምረዋል። በተጨማሪም "…. ለቻሪቲ ኮሚሽን ያቀረቡት የሐሰት ክስ ስህተት መሆኑን አምነው ይቅርታ እስካልጠየቁ ድረስ ከማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የታገዱ መሆኑን እንገልጻለን ይላል።" በመሠረቱ እንደ ውስጠ ደንቡ ካህንን ከአገልግሎት እንዲታገድ ውሳኔ የሚሰጠው የካህናት ጉባኤ ሲሆን አስፈጻሚው ደግሞ ሰ/አ/ጉባኤ ነው። ከላይ እንደገለጽኩት ይህ ኮሚቴ ከፈረሰ 2 ዓመታት ሆኖታል። የሚገርመው ይህ ደብዳቤ በስተ መጨረሻ ላይ ግልባጭ ለቁጥጥር ኮሚቴና ለዚሁ ለሌለ ኮሚቴ ተደርጓል። ለመሆኑ ይህ ካህናቱ የጻፉት ደብዳቤ በውኑ ሐሰት ነውን? እስቲ ጠቅለል ባለ መልኩ እንመልከተው ፤

1) የሰ/አ/ጉባኤው የተመረጠበት 3 ዓመቱን ጨርሶ ከ2 ዓመታት በላይ ሆኖታል ማለትም በጠቅላላ 5 ዓመታት። ታዲያ ይኼ ውሸት ነው?
2) ከላይ የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ እንደ ገለጸው የሂሳብና ንብረት አያያዝ ችግር አለው ፤ ሐሜታን ለማስወገድ በግልጽ ሪፖርት ይቅረብ ያለውን ነው እነዚህ ካህናት መልሰው ያቀረቡት። ታዲያ ይሄ ምን ውሸት ነው?
3) አንድን የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከአገልግሎት ለማገድ የካህናት ጉባኤ ሥልጣን ሲሆን ነገር ግን የወቅቱ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳዳሪ ሕጉን በመጣስ ዲያቆን ድርሻዬን ከአገልግሎት በሥልጣናቸው አግደዋል። ታዲያ ሕግ አልተጣሰም? ይኼ ስሕተት አይደለምን?
4) ንዑሳን ኮሚቴዎች በሙሉ መፍረሳቸው እየታወቀ ፤ የሚወሰኑት ውሳኔዎች በጥምር ጉባኤ እንደተወሰነ አድርጎ ማቅረብ። ይህን ራሱን እዚሁ ለቄስ ሙሉ ብርሃን የተጻፈው ደብዳቤ ላይ የሚታይ አይደለምን? ታዲያ ይኼ ጭልጥ ያለ ውሸት አይደለምን?

5) **በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አልበኝነት የሰፈነው ዋናዎቹ ኮሚቴዎች የቁጥጥር ፣ የሕግና ሥነ ሥርዓት እንዲሁም የካህናት ጉባኤ ስለሌሉ ስለሆነ በአስቸኳይ ይቋቋሙ ማለት ጥፋት ነውን?**

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሌሎችም የፈረሙ ካህናት ተመሳሳይ የሆነ እርምጃ እንደሚገጥማቸው መገመት አያዳግትም። ነገር ግን እስከ መቼ ድረስ እንዲህ ዓይነት ድፍረትና አምባገነንነት ይቀጥላል??

የ/ሰ/አ/ጉባኤው ሥርዓተ አልበኝነት በዚህ አልቆመም ነገር ግን ባለፈው ቁጥር ፩ ላይ እንዳቀረብኩት ከሰ.ጉ.አ አባላትም እንደተረዳሁት ማንም ቢሆን ወደ ቦርድ የመለወጥ ሃሳብ ያለው የለም ነገር ግን አንዳንድ ሙሉ ያልሆኑ ወይም ለአሠራር ያላመቹ አንቀጾችን ኮሚቴ አቋቁመን ለማሻሻል እያጠናን ነው የሚል ነው። ይህ በሰኔ ወር 1998 (2006) ዓም በመለው ምዕመናን የፀደቀውን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አንዳንዶች ሕጉን ለማሻሻል እንዲያመቻቸው 2/3 ሰዎች እንደሠሩት አድርገው በማሳየት ውድቅ ለማድረግ ይሞክራሉ። ነገር ግን በማኅበረ ምዕመናኑ የፀደቀ መሆኑን ለመረዳት ካስፈለገ የካህናት ጉባኤ በ15/11/2000 ዓም ቤተ ክርስቲያኗ ከሌሎች የኢ/ኦ/ተ/ አብያተ ክርስቲያን ጋር ያላትን አቋም አስመልክቶ ያወጣው መግለጫ ገጽ 3 ላይ “....የውስጥ አስተዳደሯም ሰኔ 1998 ዓም በጠቅላላው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በጸደቀውና በወጣው የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መሆኑን የካህናት ጉባኤው በድጋሚ ያረጋግጣል...” የሚለውን ማንበብ ነው (8)። በእርግጥ የወጣው ውስጠ ደንብ እንዲሻሻል ካስፈለገ ፤ አንቀጽ 51 በሚያዘው መሠረት ሊሆን ይገባል (9)። ነገር ግን የጥምር ኮሚቴዎች አለመኖርና የሰ.ጉ.አ ራሱ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ምንም ዓይነት አንቀጽ ሆነ ዐረፍተ ነገር በዚህ ወቅት ለመለወጥ ሕጉ እንደማይፈቅድ ባለፈው ቁጥር ፩ ጽሑፍ ላይ ገልጫለሁ። ነግር ግን ሕጉን ያወጡት 2/3 ሰዎች ናቸው ብሎ ዓይን ያወጣ ውሸት ፣ ሕጉ በፊትም ችግር ስላላበትና ሙሉ ስላልሆነ ከሥርዓት ውጭ በሆነ እንደ ፈለግን መቀየር እንችላለን ብሎ መበጥበጥ ፤ ዓይን አውጣነትና ሥርዓተ አልበኛ መሆን ነው።

የሆኖ ሆኖ በአጋጣሚ አሁን ሕግ እያረቀቅን ነው የሚለው ኮሚቴ ለጥናት ያዘጋጀው የኮሚቴዎች አወቃቀር flow diagram አግኝቼ እንዳየሁት ፤ ይህን ሕግ የሚያወጡ ሰዎች አእምሮ ብስለት አጠያያቂ እንዲሆን አድርጎታል (10)። እንደ flow diagram ከሆነ “ቅሬታ ሰሚ ክፍል” በሙሉ ኮሜቴዎችን ያስተዳድራል ማለት ነው። የ/ሰ/አ/ጉባኤው ምን ሊሠራ እንደታሰበ ግራ የሚያጋባ ነው። ቅሬታን ፣ጤና እና ደህንነትን በተመለከተ የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ሥራ ድርሻ ነው<u>(መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ 5 አንቀጽ 27)።</u> በተጨማሪም አቶ ግታቸው በሻውረድ የተባለው የቦርድ አሠራር ሐሳብ ዋና ደጋፊ/ተከራካሪ ያቀረበው መንደርደሪያ ሐሳብ ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ላለፉት 30 ዓመታት ከሕግ ውጭ እንደሆነች ለማሳየት ይሞክራል። የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴም በኅዳር 28 ቀን 2001 ለሰ/አ/ጉባኤ በጻፈው ደብዳቤ ላይ አቶ ጌታቸው በሻውረድ ያቀረበው ቁንጽል ሐሳብ መርዝ እንደሆነና ቤተ ክርስቲያናችንን ወደ በለጠ የማያስፈልግ ግጭት ውስጥ እንደሚከታትና ተቀባይነት እንደሌለው ውሳኔ አስተላልፏል (11)። በሌላ ሀገር ያሉ በቦርድ የሚተዳደሩ አብያተ ክርስቲያናት ወደ ሰ/አ/ጉባኤ አመራር ሲመጡ ፤ በአንጻሩ እንደ አቶ ጌታቸው በሻውረድ ያሉት ደግሞ በቦርድ ካልሆንን

ብለው ቦታውን ማመስ አሳዛኝ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን መጀመሪያ በቻሪቲ ከተመዘገበችበት ከ1989 (እ.አ.አ) ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ምንም ችግር ወይም የምትመሩበት ደንብ ትክክል አይደለም የሚል ከቻሪቲ ኮሚሽን ቀርቦብን አያውቅም። ታዲያ ይህ አላስፈላጊ የሆነ ጭቅጭቅ ለምን በዚህ ወቅት ያስፈልጋል።

መተዳዳሪያ ደንቡ መጀመሪያውኑ ሲሠራ ከብዙ አንፃር ታይቶ ለቻሪቲ ኮሚሽን የሚላኩት አባላት እንዴት እንደሚመረጡ በግልጽ ተቀምጧል ሆኖም እስከ አሁን አልተሠራበትም። ይህ የምግባረ ሠናይ ኮሚቴ በሰ/አ/ጉባኤ ሥር ሲሆን ፤ ለቻሪቲ የሚላኩትም የዚህ ኮሚቴ አባላት ናቸው እንጂ ሙሉ የ/ሰ/አ/ጉባኤ አባላት አይደሉም ፤

4. <u>**የምግባረ ሠናይ ኮሚቴ አባላት ዓይነትና ብዛት ነው (መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ 3 አንቀጽ 8/4)።**</u>

የቤተክርስቲያኑ የምግባረ ሠናይ ኮሚቴ ከሰበካው አስተዳደር ጉባኤ አባላት መካከል ከሚሰየሙት ሦስት አባላት ጋር ከአምስት ያላነሱ ከሰባት ያልበለጡ አባላት እንደሚከተለዉ ይኖሩታል።

ሀ) የሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ም/ሊቀመንበር —— የኮሚቴዉ ሰብሳቢ

ለ) የሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ገንዘብ ቤት ——— የኮሚቴዉ ገንዘብ ቤት

ሐ) የሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ 3ኛ ፈራሚ ——— የኮሚቴው ጸሐፊ ይሆናል

መ) በጠቅላላዉ ጉባኤ የሚመረጡ ካህናትና ምእመናን ——የኮሚቴዉ አባላት ይሆናሉ።

ስለ ምግባረ ሠናይ ኮሚቴ ሥራ ዝርዝር (<u>መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ 5 አንቀጽ 30/31)</u> ያንብቡ።

በጣም የሚገርመው ከቤዝ ዎተር ጀምሮ ለረጅም ጊዜ የነበረው ችግር ምርጫ ሲደርስ መመረጥ የሚፈልግ ሰው ስላልነበር ፤ የሰ/አ/ጉ አባላት ምርጫ የሚፈጸመው ቀኑን እያለፈ ነበር። በተቃራኒው አሁን ደግሞ ጭራሽ ከሥልጣን አልወርድም ብሎ እንዲያውም ሊቃወሙ ይችላሉ የሚሉትን ማስፈራራትና ከቤተ ክርስቲያን እንዳይደርሱ ማገድ ብዙ ጥያቄን ይፈጥራል። ምን ጥቅም ቢገኝ ነው እዚህ ደረጃ ላይ የተደረሰው ወይስ ተደጋግሞ የተነሣው የገንዘብ መጥፋት በርግጥ እውነተኛ ስለሆነ ለመሸፋፈን ነውን? በተጨማሪም የሰ/አ/ጉ ጊዜውን ለማራዘም ሆነ ሕግን ለመለወጥ ፣ የማይፈልጉትን ሰው ለማራቅ ፣ ድብቅ ዓላማቸውን ለማራመድ ፤ ስብሰባ ሲጠራ ቤተ ክርስቲያን ደርሰው የማያውቁ ሰዎችን ፤ ወያኔ ቤተ ክርስቲያናችንን ሊወስድ ነው በማለት እያስተባበሩ በማምጣት ቤተ ክርስቲያን ዋና የተመሠረተችበትን ዓላማዋን እንድትስት እያደረጉ ነው። የይቅርታና አደባባይ መሆኗ ቀርቶ እንደ ፖለቲካ ድርጅት ከምዕመኗ አልፈው አገልጋይ ካህናቷን ማሰናበት ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ከላይ እንደገለጽኩት ቤተ ክርስቲያን ከየትም ጎሣ ወይም የየትኛውንም ፖለቲካ ድርጅት የሚደግፍ ምዕመን ቢመጣ በሯ ክፍት ነው መጥቶ ሰውን የሚከፋፋል ነገር እስካልፈፀመ ድረስ። ይህ ዓይነት ኢክርስቲያናዊ የሆነ የተንኮል ዘመቻ ማለትም ሰውን ወያኔ እያሉ ሰውን ማጋጨትና ማባረር የተጀመረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው። ይህች ቤተ ክርስቲያን ላለፉት 20 ዓመታት አለምንም ግጭት

ወይም ረብሻ ያላለፈችበት ዓመት የለም። በተፈጠረው አለመግባባት ችግሩ ከተፈታ በኋላ ሰዎች ዕርቅ ፈጥረው አገልግሎት ቀጥለዋል እንጂ ፤ ይባረሩ ወይም በአደባባይ ይወገዙ ተብሎ ዘመቻ አልተካሄደም ምክንያቱም የክርስትናን እምነት አንዱ ትልቅ የሚያደርገው ይቅር መባባል ነውና።

በዚህች ለ/ደ/ጽ/ቅ/ማ ይሁን በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከዚህ ቀደም በደርግ ዘመነ መንግሥት ሥልጣን ላይ የነበሩ ፤ ያቺን ምስኪን ሀገር ለበለጠ ድህነት ያበቁ ፣ በብዙህ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ለስደት የዳረጉ ፣ የንፁሐንን ደም ያፈሰሱ ፣ በእስር ቤት ብዙዎችን የገረፉ ፣ ያሰቃዩ ፣ ያስለቀሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው ሲጸልዩ ለምን መጡ ብለን የተቃወመ የለም። ለምን ቢሉ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሲያስተምር "ለሕመምተኞች እንጂ ለባለ ጤናዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም.. .. ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና" ባላቸው መሠረት ስለሆነ ነው (ማቴ 9 ፤12-13)። ስለዚህ የተለያ ስም እየሰጠን ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ተሰናክለው እንዲቀሩ ማድረግ ያስፈርድብናል (ማቴ 18 ፤6-9)። *የሚገርመው እነዚህ ከላይ የገለጽኳቸው ዓይነት ሰዎች ከምዕመናኑ ምንም ቅሬታ ስላልቀረበባቸው ውለው አድረው ጭራሽ የሀገር ቤቱ አንሶ አሁንም እኛ እናውቅልሀለን ብለው ያንን ሀገራችንን ያጠፉ የአመራር ልምዳቸውን መልሰው እዚህ ሊያሳዩን ሲፈልጉ ማየት የሚያስተዛዝብ ነው።*

አለመታደል ሆኖ ኢትዮጵያውያን ስንባል በኮሚዩኒቲ ተሰባስቦ ከመረዳዳት ይልቅ መከፋፈልን ስለምንመርጥ በእንግሊዝ ሀገር ውስጥ እኛ የመጨረሻው ደረጃ የያዝን ይመስለኛል። ማኅበረሰባችን በፖለቲካውም ሆነ በኮሚዩኒቲው ባለው ክፍፍል ሕብረቱ እየጠፋ ስለሆነ በአመራር ላይ ያሉትም ሆኑ ሌሎች ወደ ቤተ ክርስቲያን በመጠጋት ያለውን አሠራር እንደ ፖለቲካው አካሄድ ሊያደርጉ ስለሚያስቡና ስለሚፈልጉ አሁን ላለው ልዩነት መፈጠር አንዱ ምክኒያት ነው ቢባል ስሕተት አይሆንም።

## ማጠቃለያ

እንግዲህ ከላይ እንደገለጽኩት ቤተ ክርስቲያናችን ብዙ ፈተና አሳልፋለች ነግር ግን እንዳሁኑ መጥፎ የሆነ ደረጃ ላይ አልደረሰችም። አሁን ያለው የካህናትና የምዕመናን ጥያቄ ግልጽ ባለ አማርኛ የሚከተለው ነው ፤

- *የሰ/አ/ጉ አስተዳደር ጊዜው ካለፈበት ከ2 ዓመታት በላይ ስላስቆጠረ በአስቸኳይ አስመራጭ ኮሚቴ ተቋቁሞ ምርጫ እንዲካሄድ ፤*
- *የሂሳብ ሪፖርት ችግር አለበት እየተባለ ከሁለት ዓመታት በላይ ሪፖርት ስላልቀረበ ፤ በአስቸኳይ ቀርቦ ግልጽ ማድረግና ያለውን ሐሜታ ማስወገድ ፤*
- *እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ለጊዜው ማድረግ ካልተቻለ ሌላው ቢቀር አጠቃላይ የምዕምናን ስብሰባ ጠርቶ ለምን እንደዘገየ ማብራሪያ መስጠትና መረጋጋትን መፍጠር ያስፈልጋል እንጂ*

*ዝም ብሎ ሌላ ሰበብና ሰዎችን የተለያየ ስም በመስጠት ጉዳዩን ለመሸፋፋን መሞከር ትዝብት ላይ የሚጥል ነው።*

አብዛኛው ነባር ምዕመናን ከሰው ላለመጋጨት ብቻ ነገሩ አሳዝኗቸው ከቤተ ክርስቲያን መራቅ ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ሌላውም ስሙ በከንቱ እንዳይጠፋ ስሕተቱ የት እንዳለ እያወቀ ከዳር ታዛቢ ሆኖ ቆሞ ፤ ሌሎች ደግሞ ዓይናቸውን በጨው ያጠቡ ከድፍረት አልፈው ምዕመናንን እያስፈራሩ ቦታውን መንፈሳዊነቱን እያሳጡ ከመጡ ውለው ሰንብተዋል። አንድ የፈላስፋዎች አነጋገር አለ “አንድ ሕዝብ የሚገባውን መሪ ያገኛል” ይላል። ስለዚህ እያንዳንዱ ምዕመን ማወቅ ያለበት ቤተ ክርስቲያናችንን ከአጋጠማት አደጋ የመጠበቅ ፣ ለእውነት ሲል መመስከር ፣ መስዋዕት የመሆን ፣ በቅንነትና በታማኝነት የሚመሩ ሰዎችን ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት መርጦ ማስቀመጥ ፣ የተሳሳቱትን የመገሰጽ ኃላፊነት ግዴታው ነው። ጌታችን እንደተናገረው በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ (ማቴ 10 ፤32) እንዳለው እያንዳንዳችን ሳንፈራ እውነቱ እንዲወጣና ፤ ሁሉም ምዕመናን ያለ ቅሬታ አብሮ በፍቅር እንዲገለገል ማድረግ ይኖርብናል። እዚህ ሀገር ላይ መጀመሪያ ክፍለ ዘመኖች ላይ እንደነበሩት ክርስቲያኖች መከራ ይደርስብናል ብለን አናስብም። እሱም ቢሆን እንኳ መከራውን ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለብን ፤ ምክንያቱም መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም በማለት ክርስቶስ ራሱ ተናግሯልና (ማቴ 10፥-38)። ስለዚህ ይህቺ ቤተ ክርስቲያን ከተዘፈቀችበት አደጋ የማውጣት የእያንዳንዱ ምዕመን ግዴታ ነው። ይህን ለማድረግ ቅዱስ አምላክ የማስተዋል አእምሮውን ይስጠን።

ሰኔ 2003

በእደ ማርያም እጅጉ